ከቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት ዓ/ አቀፍ ማህበር የተሰጠ መግለጫ

18/04/2008 ዓ ም

※ አንድነት ኃይል ነው!!!!

ከቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት ዓ/ አቀፍ ማህበር

የተሰጠ መግለጫ !!!!

የኢትዮጵያ ህዝብ ያሰኘዉን ያክል ቢደኽይም ወይም ኋላ ቀር ነው ቢባልም ለነፃነቱ፤ ለአንድነቱና ለግዛት አንድነቱ መከበር ያለስስት ደሙን የሚያፈስ ጀግና ህዝብ ነዉ። ይህ ጀግንነት ደግሞ አንደተረት በአፍ ተነግሮ የሚያበቃ ሳይሆን በመተማ፤ በአድዋ፤ በማይጨዉ፤ በወልወል፤ በፊልቱና በጎዴ ወዘተ የጦር ሜዳዎች ሊወጉትና ሊወሩት የመጡ ጠላቶቹ ጭምር የመሰክሩለት የታሪክ ሐቅ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከጀግንነቱ ጋር አርቆ አስተዋይና ታጋሽ ህዝብ ነዉ፤ ሆኖም ይህንን ህዝብ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ በተከታታይ የገዙትን የገዢ መደቦች ጀግንነቱን ለራሳቸዉ ክብርና ዝና ታጋሽነቱን ደግሞ ለስልጣን ዘመናቸዉ ማራዘሚያ አድርገዉ የመከራ ዘመን እያስቆጠሩ ኖረዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽ ህዝብ ቢሆንም እርግጫዉና ጭቆናዉ በበዛበት ቁጥር አምርሮ የሚነሳ ለገዢ መደቦች የማይመች ቁጡና እልህኛ ህዝብ መሆኑንም በተከታታይ አሳይቷል። አሁንም እንደትላቱ በሰሞኑ በወያኔ ላይ ያደረገው በአራቱም ማዕዘናት ባካሄደዉ ህዝባዊ አመጽ አሳይቷል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጀግና ነዉ፤ ተጋሽ ነዉ፤ ወይም አርቆ አስተዋይ ነዉ ሲባል እንዚህ እሴቶች ወንዱን፤ ሴቱን፤ ምሁሩን፤ ገበሬዉን፤ ሰራተኛዉንና መለዮ ለባሹን ሁሉ የሚያጠቃልሉ ህዝባዊ እሴቶች ናቸዉ እንጂ የአንድ ህብረተሰብ ክፍል ልዩ ንብረቶች አይደሉም። ሆኖም በዚህ 25 ዓመታት የወያኔ አገዛዝ ወቅት የተነሱትን ህዝባዊ የነጻነት ንቅናቄዎች /ህዝባዊ አመጾችን/ ከትግል ሜዳ እስከ ፖለቲካ ስልጣን አደባባዮች ድረስ አቀነባብሮ የሚመራ የተደራጀ ህዝባዊ ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት በየግዜው በመንገድ ላይ እየተቀጩ የሚቀሩበት አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል።

የሰሞኑም የህዝብ እንቅስቃሴ አስረግጦ አስተምሮን ያለፈውም ይህንኑ እውነታ መሆኑን መረዳት ብዙ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም!!!አንድነት ሀይል ነው!! አንድ ከሆንን የወያኔን ተንኮልና ሴራ እንበጣጥሰዋለን !! ኢትዮጵያዊያንና ህዝቧን ከሞት ፣ከመገነጠል እናድናለን የህዝብንና የሀገርን እንድነትና ሉአላዊነት እናስከብራለን፣ህዝብን ከረሀብ፣ከስደት፣ከእስርና እንግልት እንታደጋለን። አንድ ሀገር አንድ ሰንደቃላማ!! አንድ ህዝብ!! ታፍራና ተከብራ የኖረችውን ሀገራችንን ከገባችበት ማጥ ውስጥ እናወጣለን እኛም ነፃ እንወጣለን።

በመሆኑም እኛ የቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት ዓለም ዓቀፍ ማህበር አባላት ዛሬም እንደትላቱ ከአንድነት ኃይል ጋራ ተባብረን ማንኛውንም መሰሰዓትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን በማህበራችን ስም ለማላው ህዝባችን ቃል እንገባለን!!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

የቀድሞ የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት ዓ/ አቀፍ ማህበር